Young Lives | educational initiatives | ኢልምኢ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት(ኢ.ል.ም.ኢ.) | EDRI Ethiopian Development Research Institute (EDRI)

# SUBJECT: AMHARIC

# LANGUAGE: AMHARIC

## THIRD ETHIOPIA SCHOOL SURVEY
## WAVE: 2

## መመሪያ ለተማሪዎች

እያንዳንዱ ጥያቄ 1 ነጥብ ይዟል፡፡

በዚህ የፈተና ጥራዝ ያሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ አንብብ/ቢ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ፣ "ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ" የሚሉ አራት ምርጫዎች አሉ፡፡ ከምርጫዎች መካከል አንዱ ብቻ ትክክል ነው፡፡

በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ከእያንዳንዱ ጥያቄ ጋር የሚጣጣመውን ተራቊጥር በመፈለግ ትክክለኛውን መልስ በያዘው ፊደል ላይ ይህን (O) የጭረት ምልክት አድርግ/ጊ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 33. | ሀ | ለ | (ሐ) | መ |

ስህተት ለማስተካከል ሳጥኑን ሙሉ በሙሉ አጥቁር/ሪ እና ትክክለኛውን መልስህን/ሽን ይህን (O) የጭረት ምልክት በማድረግ አሳይ/ዩ፡፡ ምሳሌ፦

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 33. | (ሀ) | ለ | [redacted] | መ |

በእያንዳንዱ ትክክለኛ ጥያቄ ተራቊጥር ላይ (O) የጭረት ምልክትህ/ሽን በጥንቃቄ አድርግ/ጊ፡፡

**1** አሁን ስንት ሰዓት ነው?

- **ሀ** አሁን  አራት ሰዓት ተኩል ነው::
- **ለ** ስድስት ኪሎ ሜትር ነው::
- **ሐ** ሁለት ሳምንት ሆኗል ::
- **መ** ዛሬ ሰኞ ነው::

**2** በ7A ክፍል ውስጥ ስንት ተማሪዎች ______________ ?

- **ሀ** አለ
- **ለ** ነች
- **ሐ** አሉ
- **መ** ነው

**3** ዛሬ ______________ ስብሰባዎች አሉሽ?

- **ሀ** መቼ
- **ለ** የማን
- **ሐ** ስንት
- **መ** ማን

**4** መሀመድ ______________ ይፅፋል?

- **ሀ** ልብስ
- **ለ** ቦረሳ
- **ሐ** ደብዳቤ
- **መ** ጫማ

**5** አበባ፡- ሴትዮዋ ምን እየሰራች ነው?

አልማዝ፡- ______________________



- **ሀ** ምግብ እየበላች ነው::
- **ለ** ዉሃ እየጠጣች ነው::
- **ሐ** ልብስ እያጠበች ነው::
- **መ** መፅሃፍ እያነበበች ነው::

**6** ምግብ የሚዘጋጅበት የመኖሪያ ቤት ክፍል ምን ይባላል?

- ሀ እልፍኝ
- ለ ቆጥ
- ሐ ማድቤት
- መ መኝታ ቤት

**7** ቁርስህን በልተህ እጅህን ______________ ፡፡

- ሀ ታጠብ
- ለ ቁረጥ
- ሐ ለካ
- መ አንብብ

**8** ደምሰው በደረሰበት የመኪና አደጋ ምክንያት ሁለት እግሮቹን አጥቷል፡፡

ከሚከተሉትውስጥ የደምሰውን የጤና ሁኔታ በትክክል የሚገልፀው የቱ ነው?

ደምሰው ______________ ነው

- ሀ መስማት የተሳነው
- ለ እግረ ቆራጣ
- ሐ አካል ጉዳተኛ
- መ አይነ ስውር

**9** የእንጀራ መጋገሪያው ______________ ተሰበረ፡፡

- ሀ ወንበር
- ለ ምጣድ
- ሐ ወፍጮ
- መ ጠረጴዛ

**10** በስዕሉ ላይ ስለሚታየው ትክክል የሆነው የቱ ነው?



- ሀ ጥላውን የዘረጋችው ዝናብ ለመከላከያ ነው፡፡
- ለ ጥላውን የዘረጋችው ፀሐይ ለመከላለከል ነው፡፡
- ሐ ጥላውን የያዘላት ልጇ ነው፡፡
- መ ጥላውን አጥፋ እቦርሳዋ ውስጥ እየከተተች ነው፡፡

**11** ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክሉ የቱ ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ | አለሙ ቡና በላ:: |
| ለ | እነሱ ከገበያ መጣ:: |
| ሐ | አበበ እንጀራ ጠጣ:: |
| መ | ከበደ ዛፍ ቆረጠ:: |

**12** አለሙ:- ይቅርታ! ሚኒሊክ ትምህርት ቤት የት ነው?

በቀለ:- መጀመሪያ ቀጥታ ሂድ እና ወደቀኝ _______________ ::

| | |
|---|---|
| ሀ | ብረር |
| ለ | ታጠፍ |
| ሐ | ቁም |
| መ | ሩጥ |

**13** በስዕሉ ላይ የሚታየው ተማሪ



| | |
|---|---|
| ሀ | በመንገደኛ ማቋረጫ ላይ እያለፈ ነው:: |
| ለ | እግረኛ መንገድ ላይ ቆሟል :: |
| ሐ | በመኪና እየሄደ ነው:: |
| መ | መኪና እየነዳ ነው:: |

**14**

> አሰፋ ከሀሰን ሱቅ ቀይ ሸራ ጫማ በመቶ ብር ገዛ:: ጓደኛው በለጠም ተመሳሳይ ሸራ ጫማ በ 80 ብር ገዛ::

ከላይ በሳጥኑ ውስጥ በተሰጠው መረጃ መሰረት ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ | አሰፋ የገዛው በርካሽ ዋጋ ነው:: |
| ለ | በለጠ የገዛው በርካሽ ዋጋ ነው:: |
| ሐ | አሰፋ የገዛው ከመርካቶ ነው:: |
| መ | በለጠ የገዛው ሸራ ጥቁር ነው:: |

**15** ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛ ሀሳብ የያዘው የቱ ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ | ከበደ በግ ጠምዶ መሬቱን አረሰ:: |
| ለ | አለሚቱ እህሉን በፍየል ጭና ሄደች:: |
| ሐ | ዶሮዋ አራት ግልገል ወለደች:: |
| መ | ሰለሞን መኪና እየነዳ መጣ :: |

16 አለሚቱ፡- በቀለ የምትኖረው ከ ማን ጋር ነው?

በቀለ፡- ከእናቴ ወንድም ጋር ነው፡፡

- ሀ በቀለ ከአክስቱ ጋር ይኖራል፡፡
- ለ በቀለ ከአጎቱ ጋር ይኖራል፡፡
- ሐ በቀለ ከአያቱ ጋር ይኖራል፡፡
- መ በቀለ ብቻውን ይኖራል፡፡

<u>ከተራ ቁጥር 17-18 ያሉት ጥያቄ ያሉትን ጥያቄዎች ከታች በተሰጠውን ምንባብ መሠረት አድርጋችሁ መልሱ፡፡</u>

ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ለግንባታ የሚያገለግል ጥሩ ሲሚንቶ ያመርታል፡፡ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ሲሆን ብዙ ደንበኞች አሉት፡፡ በአዲስ አበባ እና በሌሎች ዋና ከተማዎች ውስጥ ወኪል አከፋፋዮች አሉት፡፡ በነሱ አማካኝነት ምርቱ ቶሎ ቶሎ ይሸጣል። ለብዙ ሰዎች የስራ ዕድል ከፍቷል፡፡

17 ከሚከተሉት ውስጥ ስህተት የሆነው የቱ ነው?

- ሀ ፋብሪካው ስንዴ መፍጨት ዋና ስራው ነው፡፡
- ለ የሚገኘው ኦሮሚያ ክልል ውስጥ፡፡
- ሐ ምርቱ ለግንባታ አገልግሎት ይውላል፡፡
- መ ደንበኞቹ ብዙ ናቸው፡፡

18 ፋብሪካው <u>ወኪል አከፋፋዮች</u> አሉት ሲል የተሰመረበት ቃል ምን ማለት ነው?

- ሀ የተቀጠሩ የጉልበት ሠራተኞች፡፡
- ለ ተረክበው የሚያሠራጩ ነጋዴዎች፡፡
- ሐ ጠንካራ ተቆጣጣሪ፡፡
- መ አክሲዮን የገዙ አባላት፡፡